# ለመሪው የተዘጋጀ

# (ትንቢት ምንድነው) ከተለያዩ ክፍሎች የተውጣጣ

1. ትንቢትን አለመናቅ፤ ትንቢት መመርመር ያለበት ነገር እንደሆነና መልከሙን ይዞ የማይረባውን የመጣል መብት እንዳለ ማወቅ። የሚመረመረው በእግዚአብሄር ቃል ነው። ለምሳሌ ነብይ ጌታ ነገ በ3 ሰዓት ይመጣል ብሎ ቢናገር ቃሉ ግን የሚመጣበትን ቀንና ሰዓት ማንም አያውቅም ስለሚል አንቀበለውም።
2. እግዚአብሄር ለግለሰቦች በትንቢት ሊናገር እንደሚችል እናረጋግጣለን።
3. የተነገረው ትንቢት ተፈጻሚ ከልሆነ እግዚአብሄር ስለማይዋሽ ከእግዚአብሄር አይደለም ማለት ነው።
4. መልዕክቱ ከእግዚአብሄር ይልቅ ወደሌላ ነገር የሚጠቁመን ሲሆንና ከቃሉ ጋራ የማይስማማ ሲሆን አንቀበለውም። ትንቢቱ የሚፈጸምበት ምክንያት ግን በቁ3 ላይ እንደሚናገረን እግዚአብሄር ሲፈትነን መሆኑን እናነባለን።
5. ትንቢት የሚናገረው ሰው በታማኝነት ማለትም የሰማውን ብቻ የሚያስተላልፍ መሆን ይኖርበታል። ሌላው ደግሞ እውነትም ከእግዚአብሄር የሆነ ትንቢት እንደ እሳት የሚያቃጥልና እንደመዶሻ ልብን የሚሰብር ሃይል ያለው መሆኑ ይታያል።
6. ይህ ክፍል ግልጽ ከሆነው ከእግዚአብሄር ቃል ጋር የሚቃረን ትንቢት የሚያመጣን ሰው በግልም ሆነ እንደ ቤተ ክርስትያን በግልጽ መቃወም እንዳለብን ያሳየናል።
7. ባለ ራዕዮች ራዕይን እንዳያዩ፤ ነብያቱ እውነተኛ ትንቢት እንዳይናገሩ፤ ደስ የሚያሰኘውን ነገር ብቻ እንዲነግሯቸው፤ የሚያማልለውን ነገር ብቻ እንዲተነብዩላቸው። ይህንንም የሚጠይቁበት ምክንያት ከእግዚአብሄር ጋራ ፊት ለፊት የሚያገናኛቸው ነገር ስለማይፈልጉ ነው።